
እመብርሃን

፩ አንድ አምላክ በሚሆን በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ
ስም መስከረም ፲፮ ቀን የሚነበብ የኪዳነ ምሕረት ድርሳን
ይህ ነው። ልመናዋ ፍቅሯ ከሁላችን ጋር ለዘለዓለሙ
ይደርብን አሜን።

፪ ከዚህ በኋላ እንደ ሰው ሁሉ ወደ ሰማይ ሳታርግ
በመቃብር ፈርሳ እንድትቆይ አልተዋትም እርሷ እንደ
ሰው በደካማ ተፈጥሮ አልተፈጠረችምና እንደ ሥጋዊ
ደማዊ ፍጥረት በመቃብር አልተዋትም ።

፫ ወደ ሰማይ አሳረጋት እንጂ መላእክት በሚኖሩበት
በሰማይ ቤት ኖረች።

፬ አሟሟቷም እንደ ሰው አሟሟት አይደለም ሥጋዋም
በመቃብር ተቀብሮ አልቀረም ከአረፈችበት ጀምሮ በዕፀ
ሕይወት ሥር ሥጋዋ ፯ወር ኖረ እንጂ።

፭ ሥጋዋም የተቀበረባት ምድር እንደ ማንኛውም መሬት
አይደለችም።

፮ መቃብሯም እንደቀደሙ ሰዎች መቃብር አይደለም እንደ
ነቢያት እንደ ሐዋርያት መቃብርም አይደለም እነርሱ
በሥጋ መወለዱን መስክረዋልና።

፯ እርሷ ግን ክርስቶስን በማህፀኗ ተሸከመችው። ዳግመኛ
ም የእነርሱ ተፈጥሮ በዓለም እንዳሉ ሰዎች ተፈጥሮ
ነውና።

፰ የእመቤታችን ተፈጥሮ ግን እንደዚህ አይደለም

፱ ስለዚህ የእመቤታች ሥጋ የተቀመጠው በውስጧ ገነት የሚገኝባት ልዩ ንጽሕት ያማረች በምትሆን ኤዶም በተባለች ምድር ነው።

፲ ይህችም ምድር እግዚአብሔር የፈጠረው የአባቶች አባት አዳም ከሙታን ተለይቶ የተነሣባት ናት ምድሪቱም ንጽሕት ልዩ ናት።

፲፩ ስለዚህ የእመቤታችንን ሥጋ በውስጧ አኖሩ በዕፀ ሕይወት ሥር ተቀመጠች ይኸውም የተድላ ደስታ ቦታ ነው።

፲፪ የገነት ምድር አዳም ከውስጧ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞቶ ተነሥቶ አዳምን ከልጆቹ ጋር እስከ መለሰበት ቀን ድረስ ሁል ጊዜ እንዳዘነችና ያን ጊዜ ፈጽማ ደስ እንደተሰኘች እነግራችኋለሁ።

፲፫ እንደዚሁም የእመቤታችን ሥጋ የተቀበረባት ምድር ፈጽማ ደስ ተሰኘች። ማኅበረ መላእክት በየነገዳቸው እየመጡ ንጽሕት ማርያምን ያመሰግኗታል።

፲፬ እነሆ የክብር ባለቤት አምላክን የወለደች የእመቤታች ክብሯን ነገርኋችሁ። የምድር አሕዛብ ሆይ ከክብሯ ብዛት የተነሣ ሰውነቴ ሁሉ እንደበት ቢሆን አካሌ በብርሃን ቢሸፈን ግማሹን ስንኳ ልናገር አልችልም ብዬ እነግራችኋለሁ። በአንደበቴ ምስጋናን እጀምር ዘንድ ነው እንጂ። ለእናንተ ድንቅ የሆነባችሁ የእመቤታችን ዕረፍትም እንዴት እንደ ሆነ አስረዳችሁ ዘንድ።

ልጆችም ሽማግሌዎችም ስለ ክብሯ መሰከሩ።

፲፭ ወደ ሐዋርያት ነገር እንመለስና ሥጋዋን ስለ ቀበሩበት
፲፮ ቦታ እንናገራለን። እነሆ ለእርሷ፣ለልጇ ወዳጇ ጌታችን **ኢየሱስ ክርስቶስ** ቸር ለሚሆን ለአባቱና **ማሕየዊ ለሚሆን ለመንፈስ ቅዱስ** ምስጋናን ልናቀርብ እኛ የተሰበሰብንበት ቦታ ይህ ነው።

፲፯ ስለዚህ ወደ **ቅድስት ቤተ ክርስቲያን** ገብተን ሥርዐተ ቅዳሴ አዘጋጅተን ምእመናንን እናቆርባቸውና በሰላም ወደ ቤታቸው ይሂዱ። **እግዚአብሔርም** አድሮባቸው ይኑር፡

፲፰ ስለ ተቀደሰችው ምድር ግን እግዚአብሔር ከፈቀደ አምላክን በወለደች **በእመቤታችን** ቃል ኪዳን ኃይል እስከ ፪ኛው ቀን እናመላክታችኋለን።

፲፱ ዛሬም ለተሰበሰቡት ሁሉ አባቶች ሐዋርያት ጽፈው በኢየሩሳሌም ካኖሩት መዛግብት ያገኘነውን እናስተምራቸዋለን።

**ግርቶስ** የተባለ **ዮሐንስና** የጌታችን **ኢየሱስ ክርስቶስ** እናት **እመቤታችን** አስቀድመው የነበሩባት ለዘለዓለሙ ክብር ምስጋና ይግባው።

፳ ዳግመኛም ቅዱስ **ቄርሎስ** ከዕለታት አንድ ቀን የቅዱሳን አባቶች መጻሕፍትን ሳነብ **እመቤታችን** ልጇ **ኢየሱስ ክርስቶስ** እንደ ተነሣ በእውነት ከሙታን ተለይታ እንደተነሣች የሚናገር መጽሐፍት አገኘሁኝ አለ። ይህችም ቃል ሐሰትና ምትሐት አይደለችም።

፳፩ ዳግመኛም ወደ ሐና ዕንሰት እንመለስና ሐና ነሐሴ ፯ቀን ፀነሰች።

፳፪ በዚህም ቍጥር የእመቤታችን ማርያም ልደቷ ግንቦት አንድ ቀን ይሆናል።

፳፫ መስከረም ዐሥር ቀን ለቤተ እግዚአብሔር ስዕለት አድርገው የሰጡባት ቀን ነው።

፳፬ መጋቢት ፳፱ መድኀኒታችን ክርስቶስን የፀነሰችበት ነው

፳፭ ነሐሴ ፳፱ አባቶች እንደ ነገሩን ሐዋርያት የእመቤታችን ዜና ዕርገቷን ጽፈው በመጻሕፍት መዛግብት ያኖሩበት ዕለት ነው። ከሐዋርያትም በኋላ የተነሡ ሰዎች ስለ እመቤታችን ለልጅ ልጅ ያስተምሩ ዘንድ።

፳፮ ዳግመኛም አብሮኮሮስ የጌታ ወዳጅና ሐዋርያት ከሚሆን ከመምህሩ ከዮሐንስ እንደ ሰማው ስለ እርሷ መሰከረ። እንዲህም አለ እመቤታችን ባረፈች ገዜ ሐዋርያት ሁላቸው ተሰብስበው ገንዘው የተቀደሰ ሥጋዋን ተሸክመው ወሰደው በዮሴፍ የመቃብር ቦታ አስቀምጠው ነበር፡ ያን ጊዜ እኔ አብሮኮሮስ እነርሱን እከተል ነበር፡ ከእመቤታችንም ክብሯ ብዛት የተነሣ ሐዋርያት በተውባት ቦታ ብዙ ተአምራን አየሁኝ መላእክት ወደ ገነት አሳርገው በዕፀ ሕይወት ሥር አጠገብ አኖሯት።

፻፲ **የዕረፍቷና የዕርገቷ** ዜና እንደዚህ ነው፡ ልመናዋ ክብሯ ለዘለዓለሙ ከሁላችን ጋር ይደርብን አሜን።

፩ ልመናዋ ክብሯ ለዘለዓለሙ ከሁላችን ጋር ይደርብንና እመቤታችን ቅድስት ድንግል **ማርያም** ያደረገችው ተአምር ይህ ነው።

፪ ከብዙ ወራት በኋላ መምህሬ ዮሐንስ ወደ እኔ በማይነገር ሥልጣን መጥቶ ልጄ አብሮኮሮስ ሆይ የእናቱ ድንግል **ማርያም** ሥጋ ያለበትን ቦታ አይቼ እጅ እነሳ ዘንድ ጌታየ **ኢየሱስ ክርስቶስ** ጠራኝ አለኝ።

፫ **ክርስቶም** ኀበኘው እጅ ነሳው የሰውና **የእግዚአብሔር** ዕርቅን የሆንህ ሥጋ ለአንተ ሰላምታ ይገባል እያለ እጅ ነሳው አመሰገነው የብዙዎቹ መርከብ እናቴ **ማርያም** ሰላምታ ላንቺ ይገባሻል አሁን ግን እናቴ **ማርያም** ለአዳም መሬት ነህ ወደ መሬትነትህ ተመለስ ተብሎ ስለ ተነገረው ቃል ለጥቂት ጊዜ በመቃብር እረፊ።

፬ አሁንም እናቴ **ማርያም** ሥጋሽ ወደ መቃብር በመውረዱ አትዘኚ። እኔም እንጂ የሰማይና የምድር ንጉሥ ስሆን ሞትም በእኔ ሥልጣን ሳይኖረው እንደ ሰው ሁሉ ሞቼ ወደ መቃብር ወረድሁኝ። ዳግመኛም እኔ በፈቃዴ **በአባቴና በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ** ወደዚህ ዓለም መጥቼ በሥጋ ተወለድሁኝ አላት።

፰ አብሮክሮስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዮሐንስ ጋር ወደ ገነት ሂዶ የእናቱን የእመቤታችንን ሥጋ እንደጎበኘ ተገልጾለት አየ። ዮሐንስና ጌታ በገነት ካለው ከሚያምረው አበባና ፍሬ መልካም ሽታ ያለውን ተክል ወስደው በእመቤታችን ሥጋ ላይ እንደ አስቀመጡ አየ።

፱ መላእክት ሊቃነ መላእክት ኪሩቤል ሱራፌል ወደ ገነት እየመጡ እግዚአብሔርንና እናቱ ማርያምን ያመሰግናሉ ይኸውም በዕፀ ሕይወት ሥር አጠገብ ነው።

፲ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስም አባቶችን ነፃ ያወጣቸቸው ይህች ናት እነሆ በአዳም ስሕተት ፈንታ ሥጋየ ወደ መቃብር እንደ ወረደ የእርሷም ሥጋ ወደ መቃብር ወረደ አለ።

፲፩ በገነትም ያሉ ዕፀዋት ጫፎቻቸውን አስረዝመው ጌታ የተናገረውን ቃል ሰሙ። በእርሱ፤ቸር በሚሆን በአባቱና በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ኀዘንና ድካም ወደ ሌለበት ወደ መንግሥተ ሰማያት ሥጋዋን እስከ ሚያሳርጋት ድረስ በዕፀ ሕይወት ሥር በዕፀዋት መካከል አኖራት ልመናዋ ክብሯ ለዘለዓለሙ ከሁላችን ጋር ይደርብን አሜን።

# መጽሐፈ ስንክሳር



መስቀል መልዕልተ ኵሉ ነገር
ያድኅነነ እምፀር
(ቅ/ያሬድ)

ከሁሉ በላይ የሆነ መስቀል
ከጠላት ያድነናል
(ቅ/ያሬድ)

# በግዕዝና በአማርኛ

## ከመስከረም እስከ የካቲት

ሰይ፣ወኢምንተኒ፣መባልዕተ፣ሰብእ፣አላ፣ ኮነ፣ዘይሴሰይ፣ማዕረ፣ንስቲተ፣ዘረከበ፣ በገዳም።

፲፫፤ እስመ፣ሲሳዩሰ፣ኮነ፣ዝክረ፣ስሙ፣ለእግዚእነ፣ኢየሱስ፣ክርስቶስ፣ሎቱ፣ስብሐት፣ ወተመሰሎሙ፣ለመላእክት፣ዘኮነ፣ሲሳዮሙ፣ ስብሐተ፣እግዚአብሔር።

፲፬፤ ወደልዎ፣ከመ፣ያንሶሱ፣ላዕለ፣ማየ፣ፈለግ፣ ዘይሰመይ፣አሎን፣ወኢርሕሳ፣እገሪሁ፣ እስመ፣ኮነ፣ሥጋሁ፣ይቡሰ፣ፈድፋደ፣ እምብዝኀ፣ምንዳቤ፣ወክበደ፣ኀዊን፣ዘኮነ፣ ይለብስ፣ዲበ፣ሥጋሁ፣በኵሉ፣መዋዕለ፣ ሕይወቱ፣እስከ፣ኮነ፣ከመ፣ምትሐት፣ ዘአልቦ፣ሥጋ፣ወእምድኅረ፣አሥመሮ፣ለእግዚአብሔር፣በዘከመዝ፣ተጋድሎ፣ፈለሰ፣ ኀቤሁ።

፲፭፤ ወስብሐት፣ለእግዚአብሔር፣ኪያነኒ፣ይምሐረነ፣በጸሎቱ፣ወበረከቱ፣ትብጽሐነ፣ለዓለመ፣ዓለም፣አሜን።

ብሔርን፣የሚያገለግል፣ሆነ። ሰው፣የሚመገበውንም፣ምንም፣አይመገብም፣በዱር፣ያገኘውን፣ጥቂት፣ሣርን፣ይመገባል፣እንጂ።

፲፫፤ ደገኛው፣ምግቡ፣ግን፣ክብር፣ይግባውና፣የጌታችንንኢየሱስ፣ክርስቶስን፣ስም፣ማመስገን፣ነው። በዚህም፣ምግባቸው፣የእግዚአብሔር፣ምስጋና፣የሆነ፣መላእክትን፣መሰላቸው።

፲፬፤ አሎን፣በሚባል፣የወንዝ፣ውኃ፣ላይም፣ ይመላለስ፣ዘንድ፣ተገባው፣እግሮቹም፣አይርሱም፣ሥጋ፣እንደ፣ሌለው፣መንፈስ፣እስከሚሆን፣በሕይወቱ፣ዘመን፣ሁሉ፣ከችግር፣ ብዛትና፣ከሚለብሰው፣የብረት፣ልብስ፣ ክብደት፣የተነሣ፣ሥጋው፣እጅግ፣ደርቆ፣ የረቀቀም፣ሁኖ፣ነበርና። በእንዲህ፣ያለ፣ ተጋድሎም፣እግዚአብሔርን፣ከአገለገለው፣ በኋላ፣ወደርሱ፣ሔደ።

፲፭፤ ለእግዚአብሔርም፣ምስጋና፣ይሁን፣እኛንም፣በጸሎቱ፣ይማረን፣በረከቱም፣ትድረሰን፣ለዘላለሙ፣አሜን።

## አርኬ

ኀላም፣እብል፣ለጴጥሮስ፣ብሕትው። ኮከበ፣ጠራው። ወውስተ፣ዓለም፣ኀሩም፣እምበሊዐ፣ኀብስት፣ ወጼው። እስከ፣አስተርአየ፣በአምሳለ፣ምትሐት፣ሕስው። ተሴስዮ፣ማዕር፣አብደረ፣በበድው።

፩፣በስመ፣አብ፣ወወልድ፣ወመንፈስ፣ቅዱስ፣፩ አምላክ፣አመ፣፲ወ፯ ለመስከረም፣በዛቲ፣ ዕለት፣ኮነ፣ሕንፄሃ፣ለቤተ፣ክርስቲያን፣ ዘመቃብረ፣እግዚእነ፣ኢየሱስ፣ክርስቶስ፣ ወቅዳሴሃ፣ወዓዲ፣ለኵሎን፣መካናት፣ ቅዱሳት፣ዘውስተ፣ሀገረ፣ኢየሩሳሌም፣ዘከሠተቶን፣ዕሌኒ፣ንግሥት፣ኮነ፣ሕንፀቶን፣ወቅዳሴሆን።

፪፤ ውእቱኬ፣አመ፣ኮነ፣፳ ዓመተ፣መንግሥቱ፣ ለቈስጠንጢኖስ፣ወልዳ፣እምድኅረ፣አስተጋብአ፣ማኅበረ፣ቅዱሳን፣፫፻ቱ፣፲፰ቱ፣ወ፰ቱ፣ አበው፣በሀገረ፣ኒቅያ፣ትቤሎ፣እሙ፣ዕሌኒ፣ ቅድስት፣አ፣ወልድየ፣ኮንኩ፣ዘበጻዕኩ፣አንስ፣ ለእግዚአብሔር፣ከመ፣እሑር፣ሀገረ፣ኢየሩሳሌም፣ቅድስት፣እኅሥሥ፣ወእከሥት፣ዕፀ፣ መስቀሉ፣ለክርስቶስ፣ንጉሥ፣ስብሐት።

፫፤ ወሰሚዖ፣ቈስጠንጢኖስ፣ተፈሥሐ፣በዝንቱ፣

* * *

፩፣ አንድ፣አምላክ፣በሚሆን፣በአብ፣በወልድ፣ በመንፈስ፣ቅዱስ፣ስም፣መስከረም፣ዐሥራ፣ ስድስት፣በዚች፣ቀን፣ከጌታችን፣ኢየሱስ፣ ክርስቶስ፣መቃብር፣ላይ፣ቤተ፣ክርስቲያን፣የታነፀችበትና፣የተቀደሰችበት፣ነው። ደግሞ፣በኢየሩሳሌም፣አገር፣ንግሥት፣ዕሌኒ፣ የገለጠቻቸው፣የከበሩ፣ቦታዎች፣ሁሉ፣የተሠሩበትና፣የከበሩበት፣ሆነ።

፪፤ ይህም፣እንዲህ፣ነው፣ልጇ፣ቈስጠንጢኖስ፣ በነገሠ፣በሃያ፣ዓመት፣ቅዱሳን፣የሆኑ፣ሦስት፣ መቶ፣ዐሥራ፣ስምንት፣አባቶችን፣በኒቅያ፣ ከተማ፣ከሰበሰበ፣በኋላ፣ቅድስተ፣እናቱ፣ ዕሌኒ፣እንዲህ፣አለችው፣ልጄ፣ሆይ፣እኔ፣ ወደ፣ቅድስት፣አገር፣ኢየሩሳሌም፣በመሔድ፣ የክብር፣ንጉሥ፣የሆነ፣የክርስቶስን፣ዕፀ፣ መስቀል፣ፈልጌ፣አወጣ፣ዘንድ፣ለእግዚአብሔር፣ስዕለትን፣ተቢያለሁ።

፫፤ ቈስጠንጢኖስም፣ሰምቶ፣በዚህ፣ነገር፣ደስ፣

ነገር ፡ ወፈነዎ ፡ ምስለ ፡ ሠራዊት ፡ ብዙኃን ፡ ወወሀባ ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ ፡ ወአልባሳተ ፡ ዲባግ ፡ ክቡራተ ፡ ወይእቲ ፡ ሶበ ፡ በጽሐት ፡ ሀገረ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ተባረከት ፡ እምነ ፡ መካናት ፡ ቅዱሳት ፡ ወእምዝ ፡ ሐተተት ፡ በእንተ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ ክቡር ፡ ወማሕየዊ ፡ ወበዐቢይ ፡ ፃማ ፡ ወምንዳቤ ፡ ረከበቶ ፡ ወአክበረቶ ፡ ክብረ ፡ ዐቢየ ፡ ወሰብሐቶ ፡ በዐቢይ ፡ ስብሐት ።

፬፤ ወእምዝ ፡ አዘዘት ፡ ከመ ፡ ይሕንፁ ፡ ምሥዋዐ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ በጎልጎታ ፡ ወበቤተ ፡ ልሔም ፡ ዘውስተ ፡ በዓት ፡ ዘተወልደ ፡ ውስቴታ ፡ ዚአነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ ወበጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ ወበጌቴሴማኒ ፡ ዘተቀብረ ፡ ሥጋሃ ፡ ለእግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ወበደብረ ፡ ዘይት ፡ ወበበኵሎን ፡ መካናት ፡ ቅዱሳት ፡ ወአዘዘት ፡ ካዕበ ፡ ያሠርግውዎሙ ፡ በዕንቁ ፡ ባሕርይ ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ።

፭፤ ወሀሎ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዘስሙ ፡ አባ ፡ መቃርስ ፡ አምከራ ፡ ለዕሌኒ ፡ ንግሥት ፡ ወይቤላ ፡ ኢትግበሪ ፡ ዘንተ ፡ እስመ ፡ እምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ይመጽኡ ፡ አሕዛብ ፡ ይንግሡ ፡ ላዕለ ፡ ዝ ፡ ብሔር ፡ ወይዜውዉ ፡ ኵሎ ፡ ወያንህሉ ፡ መካናተ ፡ ወይነሥኡ ፡ ወርቀ ፡ ወብሩረ ፡ ወዕንቈ ፡ ክቡረ ፡ ዳዕሙ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ትሕንጺዮ ፡ ሕንፀተ ፡ ሠናየ ፡ ወጽኑዐ ፡ ዘኢያንቀለቅል ፡ ወዘኢይትነሠት ፡ ወዘይተርፍ ፡ እምዝንቱ ፡ ሀቢዮሙ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ።

፮፤ ወይእቲ ፡ ተወከፈት ፡ ቃሎ ፡ ወአዘዘቶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ መኳንንት ፡ ከመ ፡ ይትአዘዙ ፡ ለአባ ፡ መቃርስ ፡ ወይሕንፁ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኵሎን ፡ መካናት ።

፯፤ ወእምዝ ፡ ሶበ ፡ ተመይጠት ፡ ዕሌኒ ፡ ንግሥት ፡ ኀበ ፡ ወልዳ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ ንጉሥ ፡ አይድዓቶ ፡ ኵሎ ፡ ዘገብረት ፡ በኢየሩሳሌም ። ሰሚዖ ፡ ተፈሥሐ ፡ ፈድፋደ ፡ ወፈነወ ፡ካልአ ፡ ንዋየ ፡ ብዙኀ ፡ ወሥዩማነ ፡ ላዕለ ፡ ግብረ ፡ ሕንፀት ፡ ወአዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ከመ ፡ የሀብዎሙ ፡ ለነዳቅት ፡ ዐስቦሙ ፡ በጊዜሁ ፡ ወለእለ ፡ ይትለአኩ ፡ ለግብረ ፡ ሕንፀት ፡ በጊዜ ፡ ሠርክ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ፡ እንበለ ፡ ሕጸት ፡ እስመ ፡ ይፈርህ ፡ ከመ ፡ ኢይግዐሩ ፡ ወኢይኀዝኑ ፡ በእንተ ፡ ዐስቦሙ ፡ ወኢይትመዐዕ ፡ እግዚአብሔር ፡ ላዕሌሁ ፡ በእንተ ፡ ገዐሮሙ ።

አለው ፡ ከብዙ ፡ ሠራዊ ም ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ሰጥቶ ፡ ላካት ፡ የከበሩ ፡ የግምጃ ፡ ልብሶችንም ፡ ሰጣት ፡ እርሷም ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በደረሰች ፡ ጊዜ ፡ ከከበሩ ፡ ቦታዎች ፡ ተባረከች ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ከበረና ፡ አዳኝ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ዕፀ ፡ መስቀል ፡ መረመረች ፡ በታላቅ ፡ ድካምና ፡ ችግር ፡ አገኘችውና ፡ ታላቅ ፡ ክብርን ፡ አከበረችው ፡ በታላቅ ፡ ምስጋናም ፡ አመሰገነችው ።

፬፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ በጎልጎታ ፡ በቤተ ፡ ልሔምም ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተወለደበት ፡ ዋሻ ፡ ደግሞ ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ የእመቤታችን ፡ ማርያም ፡ ሥጋዋ ፡ በተቀበረበት ፡ በጌቴሴማኒ ፡ በደብረ ፡ ዘይትም ፡ በከበሩ ፡ ቦታዎች ፡ ሁሉ ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ መሠዊያ ፡ እንዲሠሩ ፡ አዘዘች ። ዳግመኛም ፡ በዕንቍ ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ እንዲአስጌጧቸው ፡ አዘዘች ።

፭፡ በኢየሩሳሌምም ፡ ስሙ ፡ መቃርስ ፡ የሚባል ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አለ ። እርሱም ፡ ንግሥት ፡ ዕሌኒን ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መከራት ፡ ይህን ፡ እንዲህ ፡ አትሥሪ ፡ ከጥቂት ፡ ዘመናት ፡ በኋላ ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ሊነግሡ ፡ አሕዛብ ፡ ይመጣሉ ። ሁሉን ፡ ይማርካሉ ፡ ቦታዎችንም ፡ ያፈርሳሉ ፡ ወርቁን ፡ ብሩን ፡ ዕንቍውን ፡ ይወስዳሉና ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጠንካራ ፡ የሆነ ፡ የማይናወጽና ፡ የማይፈርስ ፡ ጥሩ ፡ ሕንፃ ፡ ልታሠሪ ፡ ይገባል ፡ ከዚህ ፡ የሚተርፈውንም ፡ ለድኆችና ፡ ለችግረኞች ፡ ስጪአቸው ፡ አላት ።

፮፡ እርሷም ፡ የአባ ፡ መቃርስን ፡ ምክሩን ፡ ተቀብላ ፡ መኳንንቱ ፡ ሁሉ ፡ ለአባ ፡ መቃርስ ፡ በመታዘዝ ፡ በከበሩ ፡ ቦታዎች ፡ ሁሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ እንዲአንፁ ፡ አዘዘቻቸው ።

፯፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ንግሥት ፡ ዕሌኒ ፡ ወደ ፡ ልጅዋ ፡ ንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስ ፡ በተመለሰች ፡ ጊዜ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ያደረገችውን ፡ ሁሉ ፡ ነገረችው ፡ ሰምቶ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ፡ እንደ ፡ ገና ፡ ሌላ ፡ ብዙ ፡ ገንዘብና ፡ ሕንፃውን ፡ ተቆጣጣሪው ፡ የሚሆኑ ፡ ሹሞችን ፡ ላከ ፡ ለሚገነቡና ፡ ለሕንፃው ፡ ሥራ ፡ ለሚአገለግሉ ፡ ሁሉ ፡ ደመወዛቸውን ፡ ሳያጓድሉ ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ማታ ፡ እንዲሰጧቸው ፡ ንጉሡ ፡ አዘዘ ። ስለ ፡ ደመወዛቸው ፡ እንዳይጮኹና ፡ እንዳያዝኑ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ ጩኸታቸው ፡ በእርሱ ፡ ላይ ፡ እንዳይቆጣ ፡ ይፈራልና ።

፰፤ ወእመ ፡ ፴ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለቈስጠንጢኖስ ፡ ንጉሥ ፡ ጻድቅ ፡ ሶበ ፡ ፈጸመ ፡ ሕንፀቶን፡ለመካናት፡ቅዱሳት፡ፈነወ፡ንዋየ፡ቅድሳት ፡ ወአልባሳተ ፡ ዘዲባጋት ፡ ክቡራተ ፡ ዘዕፁብ፡ሤጡሙ።

፱፤ ወፈነወ፡ዓዲ፡ኀበ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡ቍስጥንጥንያ ፡ ከመ ፡ ይንሣእ ፡ ኤጲስቆጶሳቲሁ ፡ ወይደለው፡ወከማሁ፡ኀበ፡ሊቀ፡ጳጳሳት፡ዘአንጾኪያ ፡ ወኀበ ፡ አባ ፡ አትናቴዎስ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት፡ዘሀገረ፡እስክንድርያ፡ከመ፡ይንሣእ፡ኤጲስቆጶሳቲሁ ፡ ወይትጋብኡ ፡ ኵሎሙ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ ኀበ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወከመ ፡ ይቀድሱ ፡ ኵሎ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ እለ ፡ ተሐንፃ፡ውስተ፡መካናት፡ቅዱሳት።

፲፤ ወተጋብኡ ፡ ኵሎሙ ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ ንጉሥ ፡ ወነበሩ ፡ እስከ ፡ አመ ፡ ፲ወ፮ ፡ ለወርኀ ፡ መስከረም፡ወቀደስዎን፡ለኵሎን፡አብያተ፡ክርስቲያን ፡ ወምሥዋዖን ፡ ወቀደሱ ፡ ቅዳሴ ፡ ቍርባን ፡ ወመጠዉ ፡ ሥጋ ፡ ሥጢረ ፡ ቅድሳት ፡ ለኵሎሙ፡ምእመናን፡ወኮነ፡ዐቢየ፡ፍሥሓ፡በዛቲ፡ዕለት፡ዘኢኮነ፡ከማሁ፡ግሙራ።

፲፩፤ ወሖሩ ፡ በፀዊረ ፡ መስቀል ፡ ክቡር ፡ ውስተ ፡ ውእቶን ፡ መካናት ፡ ወሰገዱ ፡ በውስቴቶን ፡ ለእግዚአብሔር፡ወሰብሕዎ፡ወለመስቀሉ፡አክበርዎ፡ወገብኡ፡ኀበ፡በሐውርቲሆሙ፡በሰላም።

፲፪፤ ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር፡ ወበኃይለ፡ መስቀሉ ፡ ይዕቀበነ ፡ ለኵልነ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ለዓለመ፡ዓለም፡አሜን።

፰፤ ጻድቅ ፡ ንጉሥ ፡ ቈስጠንጢኖስም ፡ በነገሠ ፡ በ፴ ፡ ዓመቱ ፡ የከበሩ ፡ ቦታዎች ፡ ሕንፃቸው ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳትን ፡ ዋጋቸው ፡ ብዙ ፡ ድንቅ ፡ የሆነ ፡ የከበሩ ፡ የግምጃ ፡ ልብሶችንም ፡ ላከ።

፱፤ ደግሞም ፡ ወደ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ኤጲስቆጶሳቶቹን ፡ በመያዝ፡እንዲዘጋጅ፡እንዲሁም ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትና ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ አገር ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ወደ ፡ አባ ፡ አትናቴዎስ፡ኤጲስቆጶሳቶቹን፡በመያዝ፡ሁሉም ፡ ሊቃነ፡ጳጳሳት፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ተሰብስበው ፡ በከበሩ፡ቦታዎች፡ውስጥ፡የተሠሩትን፡ወይም ፡ የታነፁትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እንዲያከብሩ።

፲፤ ንጉሡም፡እንዳዘዘ፡ሁሉም፡ተሰበሰቡ፡እስከ፡ መስከረም ፡ ወር ፡ ዐሥራ ፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ኑረው፡በዚች፡ቀን፡ሁሉንም፡አብያተ፡ክርስቲያናት ፡ መሠዊያቸውንም ፡ አከበሩአቸው ፡ የቍርባን፡ቅዳሴንም፡ቀድሰው፡ለምእመናን ፡ ሥጋውንና፡ደሙን፡አቀበሉ፡በዚችም፡ቀን ፡ ከቶ ፡ እንደርሱ ፡ ሆኖ ፡ የማያውቅ ፡ ታላቅ ፡ ደስታን፡ሆነ።

፲፩፤ የከበረ ፡ መስቀልንም ፡ በመሸከም ፡ በነዚያ ፡ በከበሩ፡ቦታዎች፡ዞሩ፡በውስጣቸውም፡ለእግዚአብሔር ፡ ሰገዱ ፡ አመሰገኑትም ፡ መስቀሉንም ፡ አከበሩት ፡ ወደ ፡ ሀገሮቻቸውም ፡ በሰላም፡በፍቅር፡ተመልሰው፡ገቡ።

፲፪፤ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ በመስቀሉ፡ኃይልም፡ሁላችን፡የክርስቲያን፡ወገናችን፡ይጠብቀን፡ለዘላለሙ፡አሜን

## አርኬ

ሰላም፡ለኢየሩሳሌም፡ዘተሐንፀ፡መዝበራ። በጥበበ፡ቈስጠንጢኖስ፡ንጉሥ፡ወለዕሌኒ፡በምክራ። እለ፡ነጸሩ፡ሥርዓታ፡ወእለ፡ርእዩ፡ግብራ። ስብሐት፡ይብሉ፡ለክርስቶስ፡በውስተ፡ኵሉ፡አሠራ። እምነ፡ ኳለማት፡ዘአዕበያ፡ወአልዓለ፡ክብራ።

፲፫፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ አዕረፈ ፡ ጦቢት ፡ ወልደ ፡ ገባኤል ፡ እምነገደ ፡ ንፍታሌም ፡ ዘተፄወወ ፡ [illegible] ፡ ምድረ ፡ ነነዌ ፡ በእደ ፡ አሜኔሶር ፡ ንጉሠ ፡ ፋርስ።

፲፬፤ ወውእቱ ፡ ጦቢት ፡ ጻድቅ ፡ ዘየሐውር ፡ በፍኖተ ፡ ጽድቅ ፡ ወርትዕ ፡ በኵሉ ፡ መዋዕለ ፡ ሕይወቱ ፡ ወእምቅድመ ፡ ተፄውዎቱሂ ፡ ምስለ ፡

፲፫፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ በፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ አሜኔሶር ፡ እጅ ፡ ተማርኮ ፡ ወደ ፡ ነነዌ ፡ አገር ፡ የተወሰደ ፡ ከንፍታሌም ፡ ነገድ ፡ የገባኤል ፡ ልጅ ፡ ጦቢት፡አረፈ።

፲፬፤ ይህም ፡ ጻድቅ ፡ ጦቢት ፡ በሕይወቱ ፡ ዘመን ፡ ሁሉ ፡ ዕውነትና ፡ ቅን ፡ በሆነ ፡ ሕግ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ነው ፡ ከወገኖቹም ፡ ጋር ፡ ከመማ

ሕዝቡ፡ይገብር፡ምጽዋተ፡ብዙኃ፡ለጽኑሳን፡ወብዙኀ፡ጊዜ፡የሐውር፡ኀበ፡ኢየሩሳሌም፡ነሢአ፡በምረ፡አባግዒሁ፡ወዐሥራተ፡እክሉ፡ወማልስተ፡እደዊሁ፡ይሁብ፡ለነዳያን።

፲፭፡ ወይእተ፡ አሚረ፡ ኵሎሙ፡ ሕዝብ፡ ክህዱ፡ ወሦቡ፡ለበዓል፡ወለደማሊ።

፲፮፡ ወአመ፡ ተፄወዉ፡ ኀበ፡ ነነዌ፡ ሕዘቢሁ፡ ኵሎሙ፡ በልዑ፡ እምእክለ፡ አሕዛብ፡ ውእቱሰ፡የዐቅብ፡ነፍሶ፡ከመ፡ኢይብላዕ፡እስመ፡ይዜክሮ፡ለእግዚአብሔር፡በኵሉ፡ልቡ።

፲፯፡ ወአሐተ፡ ዕለተ፡ ረከቡ፡ በድነ፡ ውስተ፡ ምሥያጥ፡ ወነገርዎ፡ ወተንሥአ፡ ሶቤሃ፡ እንበለ፡ይጥዓም፡እክለ፡ወአብአ፡ውስተ፡፩ዱ፡ቤት፡እስከ፡የዐርብ፡ፀሐይ፡ወሶበ፡ዐርበ፡ፀሐይ፡ከረየ፡ምድረ፡ወቀበሮ፡ወበይእቲ፡ሌሊት፡ቤተ፡ከዊኖ፡ስኩብ፡ውስተ፡ዐረፍተ፡ዐፀድ፡እንዘ፡ክሡት፡ገጹ፡ወኢያእመረ፡ከመ፡ቦ፡አዕዋፍ፡ወእልኩ፡ኰስሑ፡ውስተ፡አዕይንቲሁ፡ወውዕየ፡አዕይንቲሁ፡ወወጽአ፡ጢስ፡እምኔሆን፡ወየራ፡ወዐቃቤ፡ሥራይኒ፡ኢበቍዖ።

፲፰፡ወበውእቱ፡ጊዜ፡ሰአለ ጦቢት፡ እግዚአብሔር፡ እንዘ፡ይብል፡ተዘከረኒ፡እግዚኦ፡ወነጽር፡ላዕለ፡ምስኪንትየ፡ወኢትዝክር፡ኃጢአትየ፡ ወኃጢአተ፡ አበውየ፡ ዘረሰይከነ፡ለተፄውዎ፡ወለተበርብሮ፡ወይእዜኒ፡በከመ፡ይኤድመከ፡ግበር፡ምስሌየ፡በቅድሜከ፡ወአዝዝ፡ዘይትሜጦ፡መንፈስየ፡ከመ፡እሠዐር፡ወእኩን፡መሬተ፡እስመ፡ይኄይሰኒ፡መዊት፡እምሐይው።

፲፱፡ወበይእቲ፡ዕለት፡በእንተ፡ዘረከባ፡ለወለተ፡ራጉኤል፡ ሣራ፡ እኩይ፡ ጋኔን፡ አስማንድዮስ፡እስመ፡አስተዋሰብዋ፡ለ፯፡ዕድው፡ሶበ፡ይበውኡ፡ኀቤሃ፡ይቀትሎሙ፡ውእቱ፡ጋኔን፡ ወበእንተዝ፡ እስመ፡ ተዓየራሃ፡ አእማተ፡ አቡሃ፡ ነበረት፡ እንዘ፡ ትበኪ፡ ወትጼሊ፡ ኀበ፡ እግዚአብሔር፡ ከመ፡ ያድኅና፡ እምትዕይርቶን፡ ወተሰምዐ፡ ጸሎታ፡ ወጸ

ረኩ፡በፊት፡ለችግረኞች፡ብዙ፡ምጽዋትን፡ይሰጥ፡ነበር፡ብዙ፡ጊዜም፡የበጎቹን፡ጠጉርና፡ከእህሉ፡ዐሥራቱን፡ይዞ፡ወደ፡ኢየሩሳሌም፡ይወጣ፡ነበር፡ከገንዘቡም፡ከሦስት፡አንዱን፡ለድኆች፡የሚሰጥ፡ነው።

፲፭፡ በዚያን፡ ጊዜ፡ ሕዝቡ፡ ሁሉም፡ ክደው፡ በዓልና፡ደማሊ፡ለሚባሉ፡ጣዖታት፡ይሠዉ፡ነበር።

፲፮፡ ወገኖቹም፡ ወደ፡ ነነዌ፡ በተማረኩ፡ ጊዜ፡ ሁሉም፡ የአሕዛብን፡ እህል፡ በሉ፡ እርሱ፡ ግን፡ ሰውነቱን፡ ይጠብቅ፡ ነበር፡ የአሕዛብን፡ መብል፡ እንዳይበላ፡እግዚአብሔርን፡ያስበው፡ነበርና።

፲፯፡ በአንዲት፡ ዕለትም፡ በአደባባይ፡ የወደቀ፡ በድን፡ አግኝተው፡ ነገሩት፡ ወዲያውኑ፡ እህል፡ሳይቀምስ፡ተነሥቶ፡ሔዶ፡ፀሐይም፡እስከሚገባ፡ ወደ፡ አንድ፡ ቤት፡ ውስጥ፡ አስገብቶ፡አኖረው፡ፀሐይ፡ሲገባም፡ቆፍሮ፡ቀበረው፡በዚያች፡ሌሊትም፡እንደ፡ኃጢአተኛ፡ሁኖ፡በእድሞ፡ሥር፡ተኝቶ፡አደረ፡በእድሞውም፡ላይ፡ወፎች፡መኖራቸውን፡ስለአላወቀ፡ፊቱን፡ገልጦ፡ሳለ፡ኵሳቸውን፡ከዐይኖቹ፡ላይ፡ጣሉበት፡ዓይኖቹም፡ተቃጠሉ፡ከእሳቸውም፡ጢስ፡ወጣ፡ታወሩም፡ባለመድኃኒትም፡ሊያድነው፡አልቻለም።

፲፰፡ በዚያንም፡ ጊዜ፡ ጦቢት፡ ወደ፡ እግዚአብሔር፡እንዲህ፡ብሎ፡ለመነ፡አቤቱ፡በቸርነትህ፡አስበኝ፡ወደ፡ችግረኛነቴም፡ተመልከት፡ ለመማረክና፡ ለመዘረፍ፡ በአደረግኸን፡በእኔና፡በአባቶቼ፡ኃጢአት፡ተበቅለህ፡አታጥፋኝ።አሁንም፡በፊትህ፡ደስ፡የሚያሰኝህን፡ነገር፡አድርግ፡ከመኖር፡ሞት፡ይሻለኛልና፡በሞት፡እሰናበት፡ዘንድ፡አፈርም፡እሆን፡ ዘንድ፡ ነፍሴን፡ የሚቀበል፡ መልአክን፡እዘዝ።

፲፱፡ በዚያችም፡ዕለት፡የራጉኤል፡ልጅ፡ሣራን፡በሞድ፡ያደረ፡ክፉ፡አስማንድዮስ፡የሚባል፡ጋኔን፡ለሰባት፡ባሎች፡አጋብተዋት፡ወደርሷ፡ሲገቡ፡ሁሉንም፡ስለገደላቸው፡ስለዚህ፡የአባቷ፡አገልጋዮች፡ያሽሟጥጧት፡ነበርና፡ከሽሙጣቸው፡ያድናት፡ዘንድ፡እያለቀሰች፡ወደ፡እግዚአብሔር፡ትለምን፡ነበር፡ጸሎቷና፡የጦቢት፡ጸሎትም፡በል

ሎተ ፡ ጦቢት ፡ ቅድመ ፡ ስብሐተ ፡ ልበዩ ፡ ለልዑል ።

፳፤ ወተዘከረ ፡ ጦቢት ፡ አሚሃ ፡ በእንተ ፡ ብሩር ፡ ዘአማኀፀነ ፡ ኀበ ፡ ገባኤል ፡ ወጸውዖ ፡ ለወልዱ ፡ ጦብያ ፡ ወይቤሎ ፡ ኅሥሥ ፡ ለከ ፡ ዓሳበ ፡ ዘየሐውር ፡ ምስሌከ ፡ ኀበ ፡ ገባኤል ፡ ከመ ፡ ትትመጦ ፡ ብሩረ ፡ ዘአማዕቀብክዎ ፡ እምቅድመ ፡ እሙት ።

፳፩፤ ወይቤ ፡ ጦብያ ፡ ኦ ፡ አባ ፡ እገብር ፡ ኵሎ ፡ ዘአዘዝከኒ ፡ ወእምዝ ፡ ወጽአ ፡ ይኅሥሥ ፡ ዓሳበ ፡ ወረከቦ ፡ ለቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ በአምሳለ ፡ ብእሲ ፡ ዓሳብ ፡ ወሖረ ፡ ምስለ ፡ ጦብያ ፡ ወሰመየ ፡ ስሞ ፡ አዛርያሃ ፡ ወፈነዎሙ ፡ ጦቢት ። ወእንዘ ፡ የሐውሩ ፡ በጽሑ ፡ ምሴተ ፡ ኀበ ፡ ፈለገ ፡ ጤግሮስ ፡ ወወረደ ፡ ጦብያ ፡ ይትሐፀብ ፡ ወሠረረ ፡ ላዕሌሁ ፡ ዐቢይ ፡ ዓሣ ፡ ወይቤሎ ፡ ሩፋኤል ለጦብያ ፡ አኀዞ ፡ ወኢትፍራህ ፡ ወጥብሖ ፡ ወንሣእ ፡ ከብዶ ፡ ወልቦ ፡ ወሐሞቶ ፡ ወገብረ ፡ በከመ ፡ አዘዞ ።

፳፪፤ ወይቤሎ ፡ ጦብያ ፡ ለሩፋኤል ፡ ኦ ፡ እኁየ ፡ አዛርያ ፡ ምንተ ፡ ይከውን ፡ ዝንቱ ፡ ሐሞተ ፡ ዓሣ ፡ ወከብዱ ፡ ወልቡ ፡ ወአውሥአ ፡ መልአክ ፡ ዘተሰምየ ፡ አዛርያ ፡ ለእመ ፡ ቦ ፡ ጋኔን ፡ ላዕሌሁ ፡ ብእሲ ፡ አው ፡ ብእሲት ፡ ያጠይሱ ፡ ሎቱ ፡ ከብዶ ፡ ወልቦ ፡ ምስለ ፡ ኀራረ ፡ ዕጣን ፡ ወለዘየራ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ይኵሕልዎ ፡ ወየሐዩ ።

፳፫፤ ወኀዕበ ፡ ተናገሮ ፡ መልአክ ፡ ከመ ፡ ያውስባ ፡ ለወለተ ፡ ራጉኤል ፡ ሣራ ፡ ወአጽንዖ ፡ ኢይፍራህ ፡ እስመ ፡ የዐቅቦ ፡ እግዚአብሔር ። ወሶበ ፡ በጽሑ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ራጉኤል ፡ ተቀበሎሙ ፡ ሣራ ፡ ወአስተፍሥሐቶሙ ፡ ወእምዝ ፡ ፈተዋ ፡ ጦብያ ፡ ወተናገሮ ፡ ለአቡሃ ፡ ከመ ፡ የሀቦ ፡ ኪያሃ ፡ አቡሃኒ ፡ ይቤሎ ፡ አስተዋሰብክዋ ፡ ለሰብዓቱ ፡ ዕደው ፡ ወሞቱ ፡ ኵሎሙ ፡ ወይቤ ፡ ጦብያ ፡ ይኩን ፡ ፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ።

፳፬፤ ወሶበ ፡ አብእዎሙ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ መርዓ ፡ ተዘከረ ፡ ቃሎ ለሩፋኤል ፡ ወአጤሰ ፡ ልቦ ፡

ዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ በጌትነቱ ፡ ልዕልና ፡ ፊት ፡ ተሰማ ።

፳፤ ጦቢትም ፡ በገባኤል ፡ ዘንድ ፡ አደራ ፡ ያስጠበቀውን ፡ የብሩን ፡ ነገር ፡ አሰበ ፡ ልጁ ፡ ጦብያንም ፡ ጠርቶ ፡ ሳልሞት ፡ በገባኤል ፡ ዘንድ ፡ አደራ ፡ ያስጠበቅሁትን ፡ ብር ፡ ትቀበል ፡ ዘንድ ፡ ከአንተ ፡ ጋራ ፡ የሚሔድ ፡ በደመወዝ ፡ የሚቀጠር ፡ አሽከር ፡ ፈልግ ፡ አለው ።

፳፩፤ ጦብያም ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ ያዘዝከኝን ፡ ሁሉ ፡ አደርጋለሁ ፡ አለ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አሽከር ፡ ሊፈልግ ፡ ሔደ ፡ ቅዱስ ፡ ሩፋኤልንም ፡ አሽከር ፡ በሚሆን ፡ ሰው ፡ አምሳል ፡ አገኘው ፡ እርሱም ፡ ከጦብያ ፡ ጋር ፡ መጣ ፡ ስሙንም ፡ አዛርያ ፡ ነኝ ፡ አለ ፡ ጦቢትም ፡ ላካቸው ። ሲሔዱም ፡ በመሸ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጤግሮስ ፡ ወንዝ ፡ ደረሱ ፡ ጦብያም ፡ ገላውን ፡ ይታጠብ ዘንድ ፡ ወረደ ። ታላቅ ፡ ዓሣም ፡ ሊውጠው ፡ ተወረወረ ፡ ሩፋኤልም ፡ ጦብያን ፡ ዓሣውን ፡ ያዘው ፡ አትፍራው ፡ እረደውና ፡ ጉበቱን ፡ ልቡንና ፡ አሞቱን ፡ ያዝ ፡ አለው ፡ እርሱም ፡ እንዳዘዘው አደረገ ።

፳፪፤ ጦብያም ፡ ሩፋኤልን ፡ አንተ ፡ ወንድሜ ፡ አዛርያ ፡ ይህ ፡ የዓሣ ፡ ሐሞት ፡ ጉበቱና ፡ ልቡ ፡ ምን ፡ ይደረጋል ፡ አለው ። አዛርያ ፡ የተባለ ፡ መልአክም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡ ጋኔን ፡ ያደረበት ፡ ሰው ፡ ወንድ ፡ ወይም ፡ ሴት ፡ ጉበቱንና ፡ ልቡን ፡ ከደቀቀ ፡ ዕጣን ፡ ጋራ ፡ ያጤሱለት ፡ እንደሆነ ፡ ጋኔን ፡ ይሸሻል ፡ ሐሞቱም ፡ ዐይናቹ ፡ የታወሩ ፡ ሰውን ቢኩሉት ፡ ይድናል ።

፳፫፤ ሁለተኛም ፡ የራጉኤልን ፡ ልጅ ፡ ሣራን ፡ ያገባት ፡ ዘንድ ፡ ተናገረው ፡ እግዚአብሔርም ፡ ይጠብቀዋልና ፡ እንዳይፈራ ፡ አጽናናው ። ወደ ራጉኤል ፡ ቤትም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ሣራ ፡ ተቀብላ ደስ ፡ አሰኘቻቸው ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ጦብያ ፡ ሣራን ፡ ወደዳት ። እርሷንም ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ አባቷን ፡ ጠየቀው ፡ አባቷም ፡ ለሰባት ፡ ባሎች አጋብቷት ፡ ሰባቱም ፡ እንደሞቱ ፡ ነገረው ፡ ጦብያም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ይሁን ፡ አለ ።

፳፬፤ ወደ ፡ ሜጉላ ፡ ቤትም ፡ በአገቧቸው ፡ ጊዜ ፡ ሩፋኤል ፡ የነገረውን ፡ ቃል ፡ አስታወሰ ፡ የዓሣ

ወከብዶ ፡ ለዓሣ ፡ ምስለ ፡ ኀራረ ፡ ዕጣን ፡ አሜሃ፡ ጕየ ፡ ጋኔን ፡ አስማንድዮስ ፡ ወአኀዞ ፡ መልአክ ፡ ሩፋኤል ፡ ወአሠሮ ፡ እስከ ፡ ለዓለም።

፳፭። ወአተወ ፡ ጦብያ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አቡሁ ፡ በፍሥሓ ፡ ነሢአ ፡ ኪያሃ ፡ ሣራሃ ፡ ብእሲቶ ፡ ወተቀበልዎ ፡ አቡሁ ፡ ወእሙ ፡ በትፍሥሕት ፡ ወሶበ ፡ ኰሐለ ፡ አዕይንቲሁ ፡ ለአቡሁ ፡ ወሐሰየ ፡ ዐይኖ ፡ ወርእየ ፡ ወልዶ ፡ በጊዜሃ ፡ ወአእኰቶ ፡ ለእግዚአብሔር። ወእምዝ ፡ ከሠተ ፡ ሎሙ ፡ ርእሶ ፡ ክቡር ፡ መልአክ ፡ ሩፋኤል ፡ ወነገሮሙ ፡ ብዙኀ ፡ ነገረ ፡ ወዐርገ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ።

፳፮። ወእምድኅረዝ ፡ ገብረ ፡ ትፍሥሕተ ፡ ጦቢት ፡ ምስለ ፡ እሊአሁ ፡ ወተነበየ ፡ በእንተ ፡ ሕማሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ውእቱ ፡ ይቀሥፈነ ፡ በኃጢአትነ ፡ ወውእቱ ፡ ይሣሃለነ ፡ ወይቤ ፡ ካዕበ ፡ ብፁዓን ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ይዜክሩ ፡ በእንተ ፡ ሕማምከ ፡ እስመ ፡ ይትፌሥሑ ፡ ብከ ፡ ርእዮሙ ፡ ኵሎ ፡ ስብሐቲከ።

፳፯። ወዓዲ ፡ ተነበየ ፡ በእንተ ፡ ሕንፀታ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ወይቤ ፡ ትትሐነፅ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በዕንቈ ፡ ሰንፔር ፡ ወበመረግድ ፡ ወበዕንቍ ፡ ክቡር ፡ አረፋቲሃ ፡ ወማሕፈዲሃኒ ፡ ወአናቅጺሃ ፡ በወርቅ ፡ ንጹሕ ፡ ወመርሕባኒ ፡ በቢረሌ ፡ ወበዕንቈ ፡ አትራኮስ ፡ ወበዕንቈ ፡ ሶፎር ፡ ይትገበር ፡ ወይብሉ ፡ በኵሉ ፡ ፍናዊሃ ፡ ሃሌ ፡ ሉያ ፡ ወይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘአልዓላ ፡ ለጽዮን ፡ እምኵሉ ፡ ዓለማት።

፳፰። ወተነበየ ፡ ካዕበ ፡ ከመ ፡ ይትመየጡ ፡ ፄዋ ፡ እስራኤል ፡ እምባቢሎን ፡ ኀበ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወአዘዞ ፡ ካዕበ ፡ ለጦብያ ፡ ወልዱ ፡ ይጻእ ፡ እምነነዌ ፡ አእሚሮ ፡ ከመ ፡ በጽሐ ፡ ምዝባሬሃ ፡ ለነነዌ ፡ ዘተነበየ ፡ ዮናስ ፡ ነቢይ ። ወይቤሎ ፡ ለወልዱ ፡ ዳግመ ፡ ርኢ ፡ አ ፡ ወልድየ ፡ ከመ ፡ ምጽዋት ፡ ታጸድቅ ፡ ወታድኅን ፡ ምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ወጽአት ፡ ነፍሱ ፡ እንዘ ፡ ሀሉ ፡ በዐራቱ ፡ በ፻ወ፶ወ፰ ፡ መዋዕሊሁ ፡ ወቀበርዎ ፡ በክብር።

ውንም ፡ ጉበትና ፡ ልብ ፡ ከደቀቀ ፡ ዕጣን ፡ ጋር ፡ አጤሰ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ አስማንድዮስ ፡ የተባለ ፡ ጋኔን ፡ ሸሸ ፡ መልአክ ፡ ሩፋኤልም ፡ ይዞ ፡ ለዘላለሙ ፡ አሠረው።

፳፭። ጦብያም ፡ ሚስቱን ፡ ሣራን ፡ ይዞ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ወደ ፡ አባቱ ፡ ቤት ፡ ተመለሰ ፡ አባትና ፡ እናቱም ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉት ፡ የአባቱንም ፡ ዐይኖች ፡ በኳለ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ጭጋግ ፡ ሁኖ ፡ ከዐይኖቹ ፡ ተገፈፈ ፡ ዐይኑን ፡ ዐሸ ፡ ወዲያውኑ ፡ ድኖ ፡ ልጁን ፡ አየ ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የከበረ ፡ መልአክ ፡ ቅዱስ ፡ ሩፋኤል ፡ ራሱን ፡ ገለጠላቸው ፡ ብዙ ፡ ነገርንም ፡ ነግሮአቸው ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ።

፳፮። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከወገኖቹ ፡ ጋር ፡ ተድላ ፡ ደስታን ፡ አደረገ ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ መከራ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፡ እርሱ ፡ በኃጢአታችን ፡ ይገርፈናል ፡ ደግሞ ፡ እርሱ ፡ ይቅር ፡ ይለናል ፡ ሁለተኛም ፡ መከራህን ፡ የሚያስቡ ፡ የተመሰገኑ ፡ ናቸው። እነርሱ ፡ ክብርህን ፡ በአዩ ፡ ጊዜ ፡ በአንተ ፡ ደስ ፡ ይላቸዋልና ፡ አለ።

፳፯። ዳግመኛም ፡ ስለ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ መታነፅ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ሰንፔር ፡ መረግድ ፡ በሚባል ፡ በከበረ ፡ ዕንቍ ፡ ትሠራለች ፡ ድልድልዋ ፡ ቅጽርዋ ፡ አደባባይዋ ፡ ደጀ ፡ ጽዋም ፡ በከበረ ፡ ዕንቍ ፡ በጠራም ፡ ወርቅ ፡ ይሠራሉ ፡ አደባባይዋም ፡ ቢረሌ ፡ አትራኮስ ፡ ሶፎር ፡ በሚባል ፡ ዕንቍ ፡ ይሠራልና ፡ በመንገድዋ ፡ ሁሉ ፡ ሁሉም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስቀድሞ ፡ የነበረ ፡ ወደፊትም ፡ የሚኖር ፡ እያሉ ፡ ያመሰግኑታል ፡ ደግሞም ፡ ከዓለማት ፡ ሁሉ ፡ ጽዮንን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ያደረጋት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ይላሉ።

፳፰። ሁለተኛም ፡ የእስራኤል ፡ ምርኮኞች ፡ ከባቢሎን ፡ ወደ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እንደሚመለሱ ፡ ትንቢት ፡ ተናገረ ፡ ሁለተኛም ፡ ደግሞ ፡ ዮናስ ፡ ከነነዌ ፡ እንዲወጣ ፡ ልጁን ፡ ጦብያን ፡ አዘዘው። ከነነዌ ፡ እንዲወጣ ፡ ልጁ ፡ ጦብያን ፡ አዘዘው ። ዳግመኛም ፡ ልጁን ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ምጽዋት ፡ እንደምታድንና ፡ እንደምታጸድቅ ፡ ተመልከት ፡ ይህን ፡ ተናግሮ ፡ በዐልጋው ፡ ላይ ፡ ሳለ ፡ በመቶ ፡ ኀምሳ ፡ ስምንት ፡ ዘመኑ ፡ አረፈ ፡ በክብርም ፡ ቀበሩት።

| | |
|---|---|
| ፳፱፤ ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ኪያነኒ ፡ ይም ሐረነ ፡ በጸሎቶ ፡ ወበረከቶ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ። | ፳፱፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ እኛንም ፡ በጸሎቱ ፡ ይማረን ፡ በረከቱም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ። |

## አርኬ

ስላም ፡ ለጦቢት ፡ መፍቀሬ ፡ ምጽዋት ፡ ዘተብህለ ። እስመ ፡ ይገብር ፡ ምጽዋተ ፡ ወብዙኀ ፡ ግህለ ። እንዘ ፡ ምስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ይሄሉ ፡ ሀገረ ፡ ነነዌ ፡ ማዕከለ ። እምከመ ፡ ረከበ ፡ በአሬ ፡ ቅቱለ ። እንበለ ፡ ይቅብሮ ፡ ኢይጥዕም ፡ እክለ ።

| | |
|---|---|
| ፴፤ ወበዛቲ ፡ ዕለት ፡ ከሰበ ፡ ኮነ ፡ ተዝካሮሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ወርቅላ ፡ ወስምዖን ፡ ወመርቄዎስ ፡ ወዖዝያኖስ ፡ ወሐሊ ፡ ወሮቂኖስ ፡ ወሉክያኖስ ፡ ወአርገዝማኖስ ፡ ወጴጥሮስ ፡ ወሐና ፡ ወዕረፍት ፡ ለአባ ፡ አጋቶን ፡ ዘተፍዕመ ፡ ዕብነ ፡ ከመ ፡ ኢይትናገር ፡ ነገረ ፡ ጽሩሀ ። ወበረከቶሙ ፡ ተሀሉ ፡ ምስሌነ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ። | ፴፡ በዚችም ፡ ቀን ፡ ዳግመኛ ፡ የቅዱሳን ፡ የወርቅላ ፡ የስምዖን ፡ የመርቄዎስ ፡ የሐሊ ፡ የሮቂኖስ ፡ የሉክያኖስ ፡ የአርገዝማኖስ ፡ የጴጥሮስ ፡ የሐና ፡ መታሰቢያቸው ፡ ሆነ ፡ ተርታ ፡ ነገርንም ፡ እንዳይናገር ፡ ድንጊያ ፡ ጉርሶ ፡ የኖረ ፡ የአባ ፡ አጋቶን ፡ ዕረፍቱ ፡ ነው ፡ በረከታቸውም ፡ ከእኛ ፡ ጋር ፡ ትኑር ፡ ለዘላለሙ ፡ አሜን ። |

## አርኬ

ስላም ፡ ለአጋቶን ፡ አምሳለ ፡ በቀልት ፡ ዘፈረየ ። ክምረ ፡ ክምር ፡ ጽድቁ ፡ እስከ ፡ አስተርአየ ። ሰዓተ ፡ ፍዳ ደይን ፡ ሶበ ፡ ውእቱ ፡ ሐለየ ። ለዘይነብብ ፡ ጽሩዐ ፡ ከመ ፡ ቦ ፡ ሥቃየ ። በከናፍሪሁ ፡ ማዕዖ ፡ ዕብነ ፡ ወደየ ።

| | |
|---|---|
| ፩፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ እምላክ ፡ አሜ ፡ ፲ ወ ፯ ለመስከረም ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ፡ በዓሉ ፡ ለመስቀል ፡ ክቡር ፡ ዘእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ። | ፩፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ መስከረም ፡ ዐሥራ ፡ ሰባት ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተሰቀለበት ፡ ለከበረ ፡ መስቀል ፡ በዓሉ ፡ ነው ። |
| ፪፤ ዝንቱኬ ፡ ዘከሠተቶ ፡ ዕሌኒ ፡ ንግሥት ፡ እሙ ፡ ለቈስጠንጢኖስ ንጉሥ ፡ ጻድቅ ። | ፪፡ ይህም ፡ የጻድቁ ፡ ንጉሥ ፡ የቈስጠንጢኖስ እናት ፡ ንግሥት ፡ ዕሌኒ ከተሠወረበት ፡ የገለጠችው ፡ ነው ። |
| ፫፤ ወሶበ ፡ ኮስተረት ፡ ወግረ ፡ ጎልጎታ ፡ ረከበቶ ፡ ለመስቀል ፡ ክቡር ፡ ወምክንያተ ፡ ከዊኖቱ ፡ ወግረ ፡ ዐቢየ ፡ እስመ ፡ ተአምራት ፡ ወመንክራት ፡ ብዙኃት ፡ ኮና ፡ ያስተርእያ ፡ እምነ ፡ መቃብሩ ፡ ወእመስቀሉ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡ እስመ ፡ ሙታን ፡ ይትነሥኡ ፡ ወመፃጉዓን ፡ ወድውያን ፡ ይትፌወሱ ፡ ኵሎሙ ። | ፫፡ የጎልጎታን ፡ ኮረብታ ፡ በአስጠረገች ፡ ጊዜ ፡ የከበረ ፡ መስቀልን ፡ አገኘችው ፡ ታላቅ ፡ ኮረብታም ፡ የሆነበት ፡ ምክንያት ፡ እንዲህ ፡ ነው ። ብዙዎች ፡ ድንቆች ፡ ተአምራት ፡ ክብር ፡ ይግባውና ፡ ከጌታችን ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመቃብሩና ፡ ከመስቀሉ ፡ የሚገለጡ ፡ ሁነው ፡ ሙታን ፡ ይነሡ ፡ ነበርና ፡ የጎበጡና ፡ በሽተኞች ፡ ሁሉ ፡ ይፈወሱ ፡ ነበር ። |
| ፬፤ ወበእንተዝ ፡ ተምዑ ፡ አይሁድ ፡ አዘዙ ፡ ወሠርዑ ፡ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ ብሔረ ፡ ይሁዳ ፡ ወኢየሩሳሌም ፡ ከመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይኬሰትር ፡ ቤቶ ፡ አው ፡ መሬተ ፡ አው ፡ እዳወ ፡ ይውግር ፡ ላዕለ ፡ መቃብሪሁ ፡ ለናዝራዊ ፡ ኢየሱስ ፡ ወነበሩ ፡ እንዘ ፡ ይገብሩ ፡ ከመዝ ፡ መጠነ ፡ ፫፻ ዓመት ፡ ወዘይፈደፍድ ፡ ወኮነ ፡ ወግረ ፡ ዐቢየ ፡ እስከ ፡ መጽአት ፡ ዕሌኒ ንግሥት ። | ፬፡ ስለዚህም ፡ አይሁድ ፡ ተቆጡ ፡ እንዲህም ፡ ሥርዓትን ፡ ሠርተው ፡ አዘዙ ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡ ሁሉና ፡ በኢየሩሳሌም ፡ ቤቱን ፡ የሚጠርግ ፡ ሁሉ ወይም ፡ አፈር ፡ ወይም ፡ ጉድፍ ፡ የሚጠርግ ፡ በናዝሬቱ ፡ ኢየሱስ ፡ መቃብር ፡ ላይ ፡ ይጥል ፡ ዘንድ ፡ እንዲህም ፡ እያደረጉ ፡ ዕሌኒ ንግሥት ፡ እስከ ፡ መጣች ፡ ድረስ ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ኖሩ ። |